ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

ነሃሴ 25ቀን 2015 ዓ.ም

**በትምህርት ዘርፉ የተወሰዱና በቀጣይ የሚተገበሩ የለውጥ አጀንዳዎች**

በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፉ ያሉ ስብራቶችን ለመቅረፍ በተለይም የትምህርት ፖሊሲውን ቀድሞ ከ1ኛ- 4ኛ የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል፣ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል፣ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል ሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም 11ኛ እና 12ኛ ክፍል መሰናዶ ትምህርት የነበረውን የትምህርት ስርዓት ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ፣ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የመካከለኛ ደረጃ እና ከ 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲሆን ከማስተካከል ጀምሮ አዲስ ስርዓተ ትምህርት በመቅረጽ በመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ በዚህ አመት ሙሉ ትግበራ የተደረገ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል የሙከራ ትግበራ ላይ የነበረው ስርዓተ ትምህርት በ2016 ሙሉ ትግበራ በቀለም ትምህርቶች የሚካሄድ ይሆናል።

በዚህ ረገድ ከመጽሃፍት ህትመትና ስርጭት ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ከመንግስት ጋር በመነጋገር በከፍተኛ ትኩረት እየተሰራ ይገኛል።

እንደ ሃገር ከፍተኛ የሞራል ውድቀት ገጥሞን የነበረውን የትምህርት ምዘናና ፈተና አስተዳደር ስርዓትን ለማስተካከል ባለፉት ሁለት ዓመታት በተሰራው ከፍተኛ ስራ ህብረተሰቡ ከፍተኛ አድናቆት የቸረው ለውጥ ተመዝግቧል ይህ ወደ ኋላ እንዳይመለስ በቴክኖሎጂ የታገዘ ፈተናን ለመስጠት በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

አሁን በሃገራችን ያሉ ትምህርት ቤቶች አብዛኞቹ ከደረጃ በታች ከመሆናቸው የተነሳ ለመማር ማስተማር ስራው ምቹ አይደሉም። በመሆኑም ይህንን ለመቅረፍ "ትምህርት ለትውልድ" የትምህርት ቤቶች መሰረተ ልማት ማሻሻል ሀገራዊ ንቅናቄን በሀገር አቀፍ ደረጃ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በተገኙበት የተጀመረው በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን ሁሉም ገንዘቡ፣ እውቀቱና ጉልበቱ ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲደግፉት የማድረግ ስራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

ከዚህም በተጨማሪ ግብዓታቸው የተሟላላቸው ከሁሉም ክልሎች በትምህርታቸወ የላቀ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ተመርጠው የሚገቡባቸው 50 ልዩ አዳሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመላ ሀገሪቱ ለመገንባት የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተሰሩ የቆየ ሲሆን በቀጣይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ግንባታቸው የሚከናወን ይሆናል።

በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የሚስተዋሉትን መሰረታዊ ችግሮች ለመፍታት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወጡ ምሩቃን ብቃታቸው የተረጋገጠና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በዚህ አመት የተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተናን በሳካ መልኩ በሁሉም የመንግስትና የግል ዩኒቨርሲቲዎች መስጠት የተቻለ ሲሆን ይህም ወደፊት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።
በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የትምህርት ፕሮግራሞች አከፋፈት ዩኒቨርሲቲዎቹ ባላቸው ከባቢያዊ ጸጋ መሰረት እንዲሆን ዩኒቨርሲቲዎችን በተልዕኮና ትኩረት መስካቸው የማደራጀት ስራ የተሰራ ሲሆን በቀጣዩ ዓመት ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን ሲቀበሉ በተለዩበት የትኩረት መስክ ይሆናል። በቀጣይም በዩኒቨርሲቲዎች የሚከፈቱ አዳዲስ የትምህርት ፕሮግራሞችም በትኩረት መስክ ልየታቸው መሰረት ይሆናል፣

ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

ቀደም ሲል በሶስት አመት የዩኒቨርሲቲ ቆይታ ይሰጥ የነበረው የቅድመ ምረቃ ዲግሪ ሰልጣኞች የሚጠበቀውን ክህሎትና ብቃት ይዘው እንዲወጡ የሚያስችል አለመሆኑ በጥናት የተረጋገጠና በትምህርት ጥራቱ ላይ አሉታዊ ችግር የፈጠረ በመሆኑ የቅድመ ምረቃ ትንሹ የዩኒቨርሲቲ ቆይታ ጊዜ ከሦስት ወደ አራት ዓመት እንዲሆን የተደረገ ሲሆን በዚህ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ የአራት ዓመት ፕሮግራም አጠናቀው ተመርቀዋል፡፡

የድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች አከፋፈትና የተማሪዎች ቅበላ በተመለከተ ሁሉም የመንግስትና የግል ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን የመግቢያ ፈተና በመስጠት መቀበል እንዳለባቸው ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን ከመጪው 2016 ጀምሮ በትምህርት ሚኒስቴር ለሁሉም የድህረ ምርቃ ፕሮግራም ተማሪዎች የመግቢያ ፈተና ተዘጋጅቶ የሚሰጥ ይሆናል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነት እንዲረጋገጥ፣ ከፖለቲካዊም ሆነ አስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው የመማር ማስተማር እና የምርምር ሥራዎችን በላቀ መልኩ መፈጸም እንዲያስችላቸው ዩኒቨርስቲዎች ራስ ገዝ እንዲሆኑ በአዋጅ 1294/2015 ጸድቋል።

በዚህም መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሃምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም ባካሄደው 23ኛው መደበኛ ስብሰባ በደንብ ቁጥር 437/2015 የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያው ራስ ገዝ ዩኒቨርስቲ እንዲሆን ተወስኗል።

ይህንንም ተከትሎ የትምህርት ሚኒስትሩ ክቡር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የመጀመሪያው የአዲሱ ራስ ገዝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ሆነው በክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብይ አህመድ ተሹመዋል።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሆኑን ተከትሎ ከተሾሙት ቻንስለር በተጨማሪም አዲስ የሥራ አመራር ቦርድ የተሰየመ ሲሆን ዩኒቨርሲቲውን በሃላፊነት ሊመሩ የሚችሉ ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንቶች በቀጣይ ይመደባሉ።


ለተጨማሪ መረጃ፡-

እሴተ የሺጥላ ከፍተኛ የኮሙኒኬሽን አማካሪ
ስልክ- 0911235322
ኢሜል--esete.yeshitla@ethernet.edu.et

አመለወርቅ ህዝቅኤል የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈጻሚ
ስልክ 0911235322
ኢሜል-- ameleworkhizkeal@ethernet.edu.et


ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION